# «ወላጆች እንደሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም»

በዚህ ዓለም ያለ አስገኝ የተገኘ ፤ ያለ ወላጅ የተወለደ ፍጡር አይገኝም በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር በመጀመሪያ የሥነ ፍጥረት ምንጮች የሆኑትን ባህርያት አስገኝቷል ። እነዚህም ፍጥረታት ተፈጥሮ በሰጣቸው ጸጋ ሲዋለዱ ሲበዙ ተመልሰውም እንዳልነበሩ ሲሆኑ ይኖራሉ ።

ከምድራውያን ፍጥረታት መካከል ከፍተኛውን ደረጃ ይዘው የሚራመዱት የሰው ወገኖች ናቸውሰዎችየመወለድና የመራባት ከዚያምበኋላየመሞትግዴታ ቢኖርባቸውም ከፋውንና በጐውን ለይተው የሚያውቁበት አእምሮ ጠባይ ስለ ተሰጣቸው በሥጋዊ ሞት ብቻ እንደ ተጠቃለሉ ሕይወታቸው አይከትምም እንደሥራቸው መጠን ዋጋቸውን ወደሚያገኙበት ዓለመ ነፍስ እንደሚተላለፉ ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዱናል ።

ግን በዚህ ዓለም ሲኖሩ ከስህተት ላይ እንዳይወድቁ ሊመሩባቸው የሚገቡ ሕግጋት ተጽፈውላቸዋል ። ለሰዎች መመሪያዎች እንዲሆኑ ከተጻፉትም ሕግጋት አንዱ የሰው ልጆች የተፈጥሮ ወገኖቻቸው የሆኑትን ሁሉ እንደራሳቸው አድርገው መውደድ እንዳለባቸው ይጠቁማሉ ፤ ይሁን እንጂ ጊዜ የማይሽረው ዘመን የማይለውጠው ደመነፍስ ባላቸው ፍጥረታት ሁሉ ጸንቶ የሚኖረው የወላጆችና የልጆች ፍቅር ብቻ ሆኖ ይገኛል ፤ ወላጆች ለልጆቻቸው የሚያደርጉትን ፍቅር ለማንም አያደርጉትም አንዳንድ ወላጆች ልጆቻቸውን ከመውደዳቸው የተነሣ ሕይወታቸውን ስለልጆቻቸው አሳልፈው ከመስጠት ወደ ኋላ አይሉም ።

ይህም ሲባል የወላጆችና የልጆች ፍቅር በሰው ወገን ብቻ የተወሰነ አይደለም እንስሳት፤አራዊት፤ አዕዋፍና የመሳሰሉትም ቢሆኑ ልጆቻቸውን ከራሳቸው አብልጠው የመውደድ ጠባይ እንዳላቸው አይጠረጠርም ከፍቅራቸውም የተነሣ እነርሱ ተርበው ልጆቻቸው ቢጠግቡ እነርሱ ሞተው ልጆቻቸው ቢድኑ ስለሚወዱ አደገኛ ጠላት ሲመጣባቸው ለልጆቻቸው አልፈው ይጋረዳሉ ፤ የልጆችና የወላጆች ፍቅር ከደም ከሥጋና ከአጥንት ጋር የተዋሃደ በመሆኑ ሊመረመር በማይቻል የተፈጥሮ ምሥጢር የተደበቀ ነው ብሎ በአንክሮ ከማለፍ በስተቀር ሌላ ማስረጃ ለማቅረብ አይቻልም ።

በተለይ የሰው ልጆች ከልጆቻቸው ጋር ያላቸው ፍቅር እጅግ በጣም የጠነከረ ቢሆንም ሳይነጣጠሉ የመኖር ዕድል የሚገጥማቸው በቁጥር ያነሡ ናቸው በግድም ሆነ በውድ ልጆች ከወላጆቻቸው ጋር ይለያሉ ከሚለዩባቸውም ምክንያቶች ሞት ችግርና በሽታና የመሳሰሉትም ናቸው በተጠቀሱትና በመሳሰሉትም ምክንያቶች ከወላጆቻቸው የተለዩ ልጆች የፈለጉትን በልተውና ጠጥተው የፈለጉትን ለብሰው ለማደግ አይችሉም ። ረኃብ ፤ ጥም ፤ እርዛት ይደርስባቸዋል ። ጤናቸው በሚገባ አይጠበቅም ፤ የትምህርት እጦት የጤና ጉድለት ስለሚደርስባቸው ኃዘን ብስጭት ፍርሃት ድንጋጤ ወዘተ- የመሳሰሉት በቀላሉ ድል ይነሷቸዋል፤ሞራላቸውም እጅግ በጣም ዝቅ ያለ ይሆናል ። ያለ ወላጅ እንክብካቤ ያደጉ ልጆች ኃዘንና ብስጭት ስለማይለዩዋቸው ከሕፃንነታቸው ጀምረው ሽክም ሆነው ከመኖራቸው በስተቀር እስከሚሞቱበት ቀን ድረስ ለሕብረተሰቡ ለሀገራቸውና ለወገናቸው የሚያበረክቱት አገልግሎት ለራሳቸውም የሚያገኙት ጥቅም አነስተኛ ነው ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ወላጆች አልባ የቀሩ ልጆች ከፍተኛ ጉዳት እንደሚደርስባቸው የሚያውቅ በመሆኑ ወደ ሰማይ ለማረግ በተቃረበ ጊዜ «ወላጆች እንደሌሏቸው ልጆች አልተዋችሁም » በማለት ለደቀ መዛሙርቱ አብሥሯቸዋል ። ዮሐ-፲፬ ፲፰ ።

ደቀ መዛሙርቱም ከኢየሱስ የተነገራቸውን ቃል አምነው ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ በ፲ኛው ቀን ድንገት እንደሚነጠቅ አውሎ ነፋስ ከሰማይ ድምፅ መጣና ተቀምጠውበት የነበረውን ቤት ሁሉ ሞላው እንሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩአቸው በእያንዳንዳቸውም ላይ መንፈስ ቅዱስ መላባቸው መንፈስ ቅዱስን ይናገሩ ዘንድ እንደሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር የሐ-ሥራ ፪-፲፩

ሐዋርያት ከኢየሱስ እርገት እስከ መንፈስ ቅዱስ መውረድ ድረስ አልተለያዩም አልተነጣጠሉም ከቦታ ወደ ቦታም አልተዘዋወሩም በተሰጣቸው የተስፋ ቃል መሠረት ሲጠባበቁ ሰንብተው አጹናኙ መንፈስ ቅዱስ ወረደላቸው በዚህም ጊዜ ወላጆች እንደሌሏቸው ልጆች ይፈሩ ይደነግጡ ይባቡም የነበሩ ወደ ድፍርት በአእምሮ ጐለመሱ በመንፈስ ታደሱ አንዲት የዕብራይስጥ ቋንቋ ብቻ ያውቁ የነበሩ የተለያዩ ቋንቋዎች ተገለጸላቸውና በማንኛውም ቋንቋ ማስተማር ጀመሩ ።

ከዚያ በኋላ ይህንን ዓለም ዕጣ በዕጣ ተካፍለው ወንጌልን ለማስተማር ተሰማሩ በሚያስተምሩበትም ጊዜ ብዙ ችግር አጋጥሟቸው ነበር ። ችግር ቢገጥማቸውም መፍትሔ ለመስጠት አልተሳናቸውም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ አብሬያችሁ እኖራለሁ ያለው አምላክ አብሯቸው ይሠራልና ማር-፲፮-፳

መንፈስ ቅዱስ ያደረበት ሰው አሁንም ቢሆን የጠነከረ ኃይል አለው ያቀደውን ዓላማ ከግቡ ለማድረስ ይችላል

ተከታዩ በ፲፭ኛው ገጽ [illegible]



www.ethiopianorthodox.org

ቤተ ክርስቲያናችን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የምትመራ ስለሆነች «ወላጆች እንደሌላቸው ልጆች አልተዋችሁም » የሚለውን አምላካዊ ቃል መሠረት በማድረግ ወላጆች የሌላቸው ን ልጆችና ረዳት ዘመድ ያጡትን ባልቴቶችና ሽማግሌዎች ታፅናናለች ።

በአሁኑ ጊዜ በሃገራችን በየቦታው ወድቀው የሚታዩት ወላጅ የሌላቸው ሕፃናት ነበሩ ቢሆንም መንግሥት ወላጅ /ያጡ ሕፃናትን በመሰብሰብ ላይ ይገኛል ። በተለይ ኅብረተሰቡን እኩል አድርጎ በመመልከት ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት በአሁኑ ጊዜ ያለወላጆች የሚገኙትን ልጆች በቸልታ ሊያልፋቸው አልፈለገም « ወላጆች እንደሌሏቸው ልጆች አልተዋችሁም» የሚለውን ቃል )መፈክር ይዞ በመነሣት ፤ ግንቦት ፪ ቀን ፲፱፻፸ ዓ/ ም/ ወላጆች የሌሏቸውን ፭ሽህ ፪፻ ልጆች ሰብስቦ ወደ ወዳጅ ሀገር ለነፃ ትምህርት ሲልክ በዚህ መንገድ ሌሎችንም ልጆች የመርዳት ዓላማ እንዳለው ጭምር ተናግሯል ። የተቀደሰ ዓላማ በመሆኑ ቤተክርስቲያንም ሆነች ሌሎች በጐ አድራጊዎች ሊተባበሩበት የሚገባ ነው ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርቱን ወላጆች እንደሌሏቸው ልጆች እንደማይተዋቸው ከመናገሩም ሌላ እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ የሥራቸው ተባባሪ በመሆን እንደሚረዳቸው ገልጾላቸዋል ። ለደቀ መዛሙርቱ የተነገረው ቃል በእነርሱ ዘመን ብቻ ተወስኖ የሚቀር አይደለም የእነርሱን ዓላማ ተከትለን ለምንሠራ ለእኛና ከእኛ ቀጥለው ለሚነሱ ሁሉ የሚተላለፍ ነው ።

መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለሐዋርያት የማጽናናት የድፍረት የተሐድሶ መንፈስን እንደላከላቸው ለእኛም እንደሚልክልን አንጠራጠርም የእግዚአብሔር መንፈስ ማደሪያ ለመሆን እንድንበቃ፥ ፍቅርን ፥ ሃይማኖትን ተስፋን ገንዘብ አድርገን አንድነታችንን አጠንክረን ሳንለያይና ሳንነጣጠል የዕለት ተግባራችን ማከናወን አለብን ከዚህም ጋር ወላጆች የሌሏቸውን ልጆች መርዳት የተፈጥሮ ግዴታችን ነው ትዕዛዙን አክብረን ሕጉን ጠብቀን ከኖርን እግዚአብሔር አምላካችን ወላጆች እንደሌሏቸው ልጆች አይተውንም ለእኛ ከኃዘናችን የሚያጽናናን መንፈሳችን የሚያድስ የድፍረት ና የተሐድሶ መንፈስን ይልክልናል ።

ልሳኑ በዛብህ



www.ethiopianorthodox.org